# ከመጻሕፍት ዓለም

**ፕሮግራም** 1

## ሃይማኖተ አበው

በዛሬው የመጻሐፍት ዓለም ፕሮግራም «ሃይማኖተ አበው» የሚባለውን የሊቃውንት መጽሐፍ እናስተዋ ውቃችሁአለን። የዚህ መጽሐፍ ባለቤቶች የቤተክርስቲያን መምህራን ሊቃውንት ናቸው። በልዩ ልዩ ዘ መንና ወቅት አሕዛብ ካነደዱት እሳት፣ ከመዘዙት የሰይፍስለት፣ ከተጋበዙበት የተራቡ አናብስት አንደበ ት የተረፈችውን ቤተ ክርስቲያን ሰይጣን በኑፋቄ ትምህርት ሊበርዝ መናፍቃንን ሲያስነሣ ሊቃውንት መጽሐፍ አልበው፣ ኃይለ ቃል ጠቅሰው፣ ተከራክረው ረትተው የቤተክርስቲያንን እውነተኛ ትምህርት የጠበቁና ያስጠበቁ መጻሕፍትን የጻፉ፣ በስንዴ መካከል የተዘራውን እንክርዳድ ለይተው ያሳዩ የቤተክ ርስቲያን ዓይኖች ናቸው።
ሃይማኖተ አበው ማለት ምን ማለት ነው?
በመጽሐፉ የተካተቱ መልእክቶች ምን ምን ናቸው?
የሃይማኖተ አበው አስተምህሮ ምንድን ነው?
መጽሐፉን ያሰባሰቡት እነማን ናቸው?
የመጽሐፉ አከፋፈል እንዴት ነው?
በሃይማኖት አበው የተካተቱ ሊቃውንት መነሻ ዘመን ከየት እስከ የት ነው?
ወደ ኢትዮጵያ መቼ መጣ?
ወደ አማርኛ መቼ ተተረጎመ?
የመጽሐፉ ጠቅላላ ይዘት ምን ይመስላል?
መጽሐፉ በቤተክርስቲያን ያለው ቦታ ምንድን ነው? የሚሉትን ጥያቄዎችና ሌሎችንም እንመልሳለን።

ሃይማኖት አበው የሚባለው መጽሐፍ የሊቃውንት መጻሕፍ፣ ወይም ድርሳን፣ መልእክት የተሰባሰበበት የአበውን ትምህርት ለትውልድ ለማስተላለፍ የወደዱ የኋላ ሰዎች ከየመጽሐፍቱ እና ከየቋንቋው ለቅ መው ፣ ተርጉመው፣ እንደፍትሐ ነገሥት ለብቻው አንድ ክፍል መጣፍ ያደረጉት ታላቅ ምእላድ ወይ ም  የተሰባሰበ መጽሐፍ  ነው። (ኪ. ወልድ ክፍሌ)። «ይህ መጽሐፍ ሃይማኖተ አበው ይባላል። ትርጓ ሜውም የአባቶች ሃይማኖት ማለት ነው... ሃይማኖተ አበው መባሉ አበው ከእግዚአብሔር ተምረው ያ መኑበት እስከ ፍጻሜ ዘመናቸው ያስተማሩት፣ያለወጡት፣ ለልጆቻቸው ያስተማሩት፣ ለልጅ ልጅ የሚተ ላለፍ፣ እስከዛሬ ያልተቋረጠ፣ ወደፊትም የማይቋረጥ መሆኑን ለማስረዳት ነው» (ሃ. አበው መቅድም) ትምህርተ ሃይማኖት በነቢያት፣ በሐዋርያት ብቻ ሳይወሰን በመምህራንና በሊቃውንት እየተራቀቀ ተላል ፎ እሰከ ዛሬ ደርሷል። ይህ መጽሐፍ ሊቃውንት ቅዱሳት መጽሐፍትን እየተረጎሙ መናፍቃንን እያሳፈ ሩ፣ እውነተኛውን ሃይማኖታቸውን ለትውልድ ያስተማሩበት መጽሐፍ ነው።

## በመጽሐፉ የተካተቱ መልእክቶች

ሃይማኖት አበው
1. የጌታን ትምህርት
2. የሐዋርያትን ትምህርት
3. በሶሥቱ ጉባኤያት ማለትም በኒቂያ ጉባኤ፣ በቁስጥንጢኒያ ጉባኤ፣ በኤፌሶን ጉባኤ የተላለፉትን ውሳኔዎች
4. ከኬልቄዶን ጉባኤ በፊት የነበሩትን ሊቃውንት ትምህርት
5. ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ በመንበረ ማርቆስ የተቀመጡትን ሊቃውንት ትምህርት ያካተተ ነው።

ትምህርቱ
1. ምሥጢረ ሥላሴ
2. ምሥጢረ ሥጋዌ
ናቸው።

1. ምሥጢረ ሥላሴ - በመልካችን በምሳሌአችን ሰውን እንፍጠር ዘፍ 1፥26 ያለውን እግዚአብሔርን በአንድነቱ በሦሥትነቱ የሚገልጥ ትምህርት ነው። በሐዲስ ኪዳንም «ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» «ስታጠምቁአቸውም በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁአቸው» ማቴ 28፥.. ብሎ መድኃኒታችን የገለጠውን ነገረ ሥላሴ አምልተው፣ አስፍተው አብራርተው ከብሉይና ከሐዲስ ለቅመውና አዋሕደው አራቀውና ተራቀው አምነውና አሳምነው የተረዱትን አሳውቀው ያልደረሱበትን አድንቀው ያስተማሩትን ትምህርተ ሥላሴ ይዞአል።

2. ምሥጢረ ሥጋዌ - «አስቀድሞ ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ… ያ ቃል ሥጋ ሆነ፤ በእኛም አደረ» ዮሐ 1፥ 1-14 ያለውን ቃል መሠረት አድርገው የክርስቶስን የሥጋዌውን ነገር አምልተውና አስፍተው አራቀውና ተራቀው ያቀረቡበት፣ ቤተክርስቲያንን ከስህተት የጠበቁበት፣ ስለ ተዋሕዶ ጠበቃ ሆነው አንቀጽ ጠቅሰው መጽሐፍ አልበው መናፍቃንን ረትተው ቤተክርስቲያንን በሃይማኖት ጠብቀው ያቆዩበትን ዋና ዋናትምህርቶችን የያዘ መጽሐፍ ነው።

<u>የመጽሐፉ አሰባሳቢዎች (አስተጋብእያነ መጻሕፍት)</u>

ሃይማኖተ አበው በየጊዜው የተነሡ ሊቃውንት ያስተማሩትን ትምህርት፣ የላኩአቸውን የትምህርት መልእክቶችና ድርሳናት ያካተተ መጽሐፍ ሲሆን መልእክቶቹን፣ ድርሳኖቹንና ትምህርቶቻቸውን ያሰባሰቡት ዮሐንስ ዘቡርልስ እና አባ ሚካኤል ዘሀገር አትሪብ ወመሊክ መሆናቸውን የሃይማኖት አበው ታሪክ ይናገራል።

<u>አከፋፈል</u>
ሁለት ዓይነት አከፋፈሎች አሉት
1. ትምህርታዊ አከፋፈል - ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው «ድርሳን» ይባላል። ሁለተኛው «ግዘት» ይባላል። ሦስተኛው «ስምዓት» ይባላል።
2. የመጽሐፉ አከፋፈል
ከመጀመሪያው እስከ ኤጲፋንዮስ ክፍል አንድ።
ከኢጲፋንዮስ እስከ ለኀበ ነገሥት ሄራን ክፍል ሁለት
ከኀበ ነገሥት ሄራን እስከ ሲኖዲቆስ ክፍል ሦስት
ከሲኖዲቆስ እስከ መጨረሻው አራተኛ ክፍል ናቸው። በዚህ መልክ መጽሐፉን የከፈሉት ግብጻውያን መሆናቸውን ታሪኩ ይናገራል።

<u>በሃይማኖት አበው የተካተቱ ሊቃውንት መነሻ ዘመን</u>
ጌታ ለሐዋርያት ያስተማረውን ትምህርት፣ ሐዋርያት የሰበኩትን መነሻ በማድረግ እስከ አስረኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሡ ሊቃውንት ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ስለ ሃይማኖት በቃል በመጽሐፍ ያስተላለፉትን ትምህርት አጠቃሎ በአጭር በአጭሩ የያዘ መጽሐፍ ነው። (መግለጫውን ይመልከቱ)

<u>ወደ ኢትዮጵያ መቼ መጣ?</u>

በሸዋ ዘመነ መንግሥት «በመብአ ጽዮን አስራተ ጽዮንም ይባላል» በእርሱ  ከአረብ ወደ ግዕዝ ተተርጉሞአል። ዓመተ ምሕረቱ በግልጽ የታወቀ አይደለም።

1. በመክስተ ዓርስቱ ላይ እንደተገለጸው መጽሐፉ ከቅብጥ ወደ ዐረብ፣ ከዐረብ ወደ ግዕዝ  ተተርጉሞአል። «ተተርጎመ እም ልሳነ ቅብጢ ለዐረብ ወይእዜኒ ተርጎምኖ እም ልሳነ አረብ ለግዕዝ በስምረቱ ወበክሂሎቱ ለእግዚአብሔር» «ከቅብጥ ወደ አረብ ተተረጎመ፤ አሁንም በእግዚአብሔር ፈቃድና በከሐሊነቱ ከዐረብ ወደ ግዕዝ ተረጎምነው» ይላል። ቅብጥ የሚባለው ቋንቋ የጥንት የግብጻውያን ቋንቋ ነበር። ዛሬ ግን ቋንቋው ጠፍቶ ፊደሉ ብቻ ቀርቶአል። ቅብጥ ማለት ኮፕት ማለት ነው።

<u>ወደ አማርኛ መቼ ተተረጎመ?</u>

ከዐረብ ወደ ግዕዝ ከተተረጎመ ከአምስት መቶ ዓመታት በኋላ ወደ አማርኛ በነጠላ ትርጉም ተዘጋጅቶአል። በመተርጉማን አባቶች ግን ራሱን ችሎ ከሌሎች የሊቃውንት መጽሐፍት ጋር ሲተረጎምና ሲነገር ኖሮአል። ስለዚህ የትርጓሜ ሥራ በታተመው የሃይማኖት አበው መጨረሻ ያለው ማስታወሻ እንዲህ ይላል። «... ይህ ሃይማኖት አበው መጽሐፍ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ለ500 ዓመታት ያህል በሥራ የቆየ ሲሆን የግዕዙ ቅጅ በእጅ ጽሕፈት በብዙ ድካም በኢትዮጵያ ገዳማትና አድባራት የሚገኝ ቢሆንም በአማርኛ የሚገኘው በትምህርት ቤት በጥቂት ቦታ ብቻ ነው። ያውም ቢሆን ኃይለ ቃሉ ከባድበመሆኑ ምክንያት ምሥጢሩን ለማስረዳት ሲባል ተደጋግሞ ተመላልሶ በሚሰጠው ብዙ አወራረድ ባለው በድርብ ወይም በእጥፍ ትርጓሜ እንጂ በነጠላ ትርጓሜ እስከ ዛሬ አልቀረበም። በነጠላ አማርኛ ትርጓሜ ግዕዝና አማርኛ ጎን ለጎን ሆኖ እየተጠባበቀ የሃይማኖትን ምሥጢር ለመግለጽ በሚችልበት ዝግጅት ለመጀመሪያ ጊዜ መቅረቡ ነው።በዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ላይ ብዙ ድካም አጋጥሞናል። አንደኛ የተጣራ የግዕዝ ንባብ ለማግኘት የታረሙ በጉባኤ ቤተ የተነበበባቸው መምህራን መላልሰው የመረመሩአቸው መጻሕፍት ያስፈልጉ ነበር።

ሁለተኛ ስለዝግጅቱ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ የተሰጠን ትዕዛዝ በነጠላ ትርጓሜ እንዲዘጋጅ ሲሆን ከዚህ በፊት ይህን መጽሐፍ በነጠላ ትርጓሜ ለማቅረብ የሞከረ ባለመኖሩ ከብዙ የትርጓሜ አወራረድ ውስጥ አንዱን መምረጥ ያውም ሆኖ ከግዕዙ ጋራ የማይስማማ ሆኖ ቢገኝ እንዲስማማ ለማድረግ .... ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ስለነበረብን ዝግጅቱ ሦስት አመት ያህል ወስዶአል። ... ሕትመቱም በልዩ ልዩ ሁኔታ ባጋጠመው ችግር ምክንያት የዘጠኝ ዓመት ዕድሜ ፈጅቶአል። የችግሩም ዓይነት የገንዘብና የወረቀት መታጣት ነው። አሁንም ሊፈጸም የቻለው ከውጭ አብያተ ክርስቲያናት በተገኘው የእርዳታ ገንዘብ ነው። ...» ካሉ በኋላ «በዚህ የሊቃውንት መጽሐፍ ዝግጅት እነ አዛዥ ላሜህን እነ አራት ዓይና ጎሹን፣ እነ መምህር አካለ ወልድን፣ እነ መምህር ሰው አገኘሁን፣ እነ መምህር እንግዳ እሸትን፣ እነ ብፁዕ አቡነ አብርሃም ቀዳማዊ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያን፣ እነ ብፁዕ አቡነ ይስሃቅን ስናስታውሳቸው የቤተክርስቲያን ከዋክብት ስለሆኑ ቤተክርስቲያን በሥራቸው ትመካለች» በማለት ባለሙያዎችን አስታውሰዋል።

በግዕዝና በአማርኛ ያዘጋጁት ሊቃውንት ለንባብ እንዲያመች ምዕራፍና ቁጥር አዘጋጅተውለታል። ከዚህ በተጨማሪ መጽሐፉ ክፍሎች ያሉት ሲሆን ክፍሎቹ የተሰጡት በቀደሙት ግብፃውያን ሊቃውንት ነበር። ስለዚህም «ክፍሎቹ ከቀድሞዎቹ ደራሲያን እንደተወሰኑ በነበሩበት የጸኑ ሲሆን አንባቢ ለመክፈል ለመመጠን እንዲያመቸው በአዲሱ ዝግጅት ምዕራፍና ቀጥር ተሰጥቶታል። በቁጥሩም ውስጥ ረዘም ያለ ንባብ ያለባቸው ቁጥሮች ይገኛሉ። ምሥጢሩን አጠቃሎ ለማግኘት ሲባል ታስቦ የተደረገ ነው» በማለት በኋላ የታከሉ መሆናቸውን ሊቃውንቱ ጠቁመዋል።

በዚህ መሠረት አንድ መቶ ሠላሳ አንድ ምዕራፎች 605 ገጽ ያለው ሆኖ ቁጥርም ተሰጥቶት በዘመናዊ መንገድ ከግዕዝ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ በሁለቱም ቋንቋዎች የሚነበበው ሃይማኖተ አበው ዛሬ በብዙ ኮፒዎች ተባዝቶ ታትሞ ለአንባብያን እና ለአብያተክርስቲያናት በመዳረስ ላይ ይገኛል።

<u>የመጽሐፉ ጠቅላላ ይዘት</u>

ሀ. ድርሳን
ለ. ቃለ ግዘት
ሐ. ስምዓት

<u>ሀ. ድርሳን</u>

ምዕራፍ አንድ የራሱ የምዕራፉ መግለጫ እና መክስተ አርዕስተ ሲሆን ከዐረብኛ ወደ ግዕዝ በተረጎሙት ሊቃውንት ወይንም መጀመሪያ ባሰባሰቡት ሊቃውንት የተዘጋጀ ነው።

ትምህርቱ ከምዕራፍ ሁለት ይጀምራል (እልመስጦአግያ) ይባላል። ይህም ማለት ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ያስተማረው የሃይማኖት ትምህርት ማለት ነው። ስለዚህ ከእልመስጦአግያ ወይም ምዕራፍ ሁለት እስከ ምዕራፍ 616 (የዘካርያስ ይህያ ድርሳን ድረስ) ያለው ጠቅላላ ድርሳን ነው። ድርሳንም ማለት ብዙ ትምህርቶችን የያዘ ከብሉይና ከሐዲስ እያጣቀሰ ስውሩን ምሥጢር የሚገልጽ በሊቃውንት የተደረሰ ትምህርት ማለት ነው።በዚህ ውስጥም 57 ድርሳናት በ57 ሊቃውንት ተዘጋጅተው ቀርበውበታል።

<u>ለ. ቃለ ግዘት</u>

ከድርሳን ቀጥሎ ያለው ክፍል ቃለ ግዘት ነው። ቃለ ግዘትም ማለት ሊቃውንት ምሥጢረ ሥጋዌና ምሥጢረ ሥላሴ ላይ የተዛባ ትምህርት ያስተማሩትን ትምህርታቸውን እያፈረሱ የቀናውን ሃይማኖት እያስተማሩ ያመኑትን እየመለሱ፣ ያላመኑትን እያወገዙ የጻፉአቸው ትምህርቶችን የያዘ ክፍል ስለሆነ ቃለ ግዘት ተብሏል። መናፍቃንን ከምእመናን የሚለይ ትምህርት ማለት ነው።
ይህም ከምዕራፍ 117 እስከ ምዕራፍ 124 ድረስ የሰባት ሊቃውትን ቃለ ግዘት ይዞ ይገኛል። እነዚህም፥

ቃለ ግዝተ ዘጎርጎርዮስ
ቃለ ግዘተ ዘባስልዮስ
» ዘጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት
» ዘቄርሎስ
» ዘቴዎዶስዮስ
» ዘዮሐንስ ናቸው።

ሐ. ስምዓት

ስምዓት ማለት ምስክርነት፣ የምስክርነት ትምህርት እውነተኛውን ትምህርት የሚያሰማ፣የሚመሰክር፣ የሚገልጽ ማለት ነው። ስምዐት የሚባለው ከምዕራፍ 124 እስከ ምዕራፍ 131 ድረስ ያሉትን ክፍሎች ይይዛል። ከምዕራፍ 126 ጀምሮ ያለው የስምዐት ክፍል ከሌላው ክፍል በተለየ መልኩ መጀመሪያ የተወሰኑ ሊቃውንት ለምሳሌ የነቄርሎስ ትምህርት ተጽፎበታል። ከዚያ በኋላ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ትምህርቶች ቃል በቃል ተወስደው ተጽፈውበታል።
በጠቅላላ በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ ድርሰቶቻቸውም በከፊል የተካተቱላቸው ሊቃውንት 57 ናቸው። በቃለ ግዘት ላይ የተካተቱትን ከላይ አስታውሰናል። በስምዐት ላይ የተካተቱት የጥቂት ሊቃውንት ምስክርነቶች እና ከሐዋርያት ሥራ፣ ከጳውሎስ መልዕክት፣ ከያዕቆብ መልዕክት፣ ከሙሴ ኦሪት፣ከዳዊት መዝሙር እና ከማቴዎስ ወንጌል የተወሰዱ ትምህርቶች ናቸው።

<u>በቤተክርስቲያን ያለው ቦታ</u>

ሃይማኖተ አበው ከብሉይ ኪዳንና ከሐዲስ ኪዳን ቀጥሎ እንደሌሎቹ የሊቃውንት መጻሕፍት የ
ትምህረተ ሃይማኖት መረጃ፣ የተሰወረ ምሥጢር የተገለጠበት፣ የሊቃውንት ሃይማኖታዊ ሃሳብ የተብራ
ራበት መጽሐፍ በመሆኑ በቤተክርስቲያን ታላቅ ቦታ አለው። ይህውም ሊታወቅ ሃይማኖተ አበው እንደ
ሌሎቹ ቅዱሳት መጻሕፍት በጉባኤ ቤት ለደቀመዛሙርት በድርብ ትርጓሜ ትምህርት ሆኖ ይሰጣል።
እርሱንና ሌሎችንም የሊቃውንት መጻሐፍት ለምሳሌ ቅዳሴያትን፣ ድርሳናትን፣ ተግሳጻትን ያጠኑ የአብ
ነት ደቀ መዛሙርት የሊቃውንት መምህራን ተብለው ጉባኤ ተክለው ለሌሎች ያስተምራሉ።

ይህም የሚያሳየን ሃይማኖተ አበው በቤተክርስቲያን ዋና የትምህርት ርዕስ ከሆኑት ዓይነተኛ ትምህርቶ
ች አንዱ መሆኑን ነው። ቤተክርስቲያን ከኑፋቄ ርቃ፣ ከመናፍቃን ተጠብቃ፣ በምሥጢረ ሃይማኖት በ
ልጽጋ እንድትኖር መጽሐፉ ጉልህ አስተዋጽዖ አለው። ይልቁንም በሶሥቱ ጉባኤያት የተወሰነውን ትም
ህረተ ሃይማኖት አጉልቶ አስፍቶ የሚያስተምር መጽሐፍ በመሆኑ ለቤተክርስቲያን ትልቅ የሃይማኖት
መጋቢ መጽሐፍ ነው። አበው ሊቃውንት በሞት ቢያልፉም የቀና ሃይማኖታቸው፣ ያስተማሩት ትምህር
ት በጻፉአቸው መጻህፍት ለልጆቻቸው እየተላለፈ እንዲኖር «በቃል ያለ ይረሳል በመጽሐፍ ያለ ይወረ
ሳል» እንዲሉ ይህ መጽሐፍ በሃይማኖተ አበው ጸንተን እንድንኖር ያስተምረናል። ይህውም ሊታወቅ
ከቁርባን በፊት በቤተክርስቲያን በዓሉን የሚመለት ኃይለ ቃል ተመርጦ ይነበባል። ያም የሆነው መጽሐ
ፉ በዕለት ከዕለት ሕይወታችን እውነተኛውን ሃይማኖት የሚያስተምር፣ አንቀጸ ሃይማኖትን የሚያብራ
ራ በመሆኑ ነው።

<u>ማጠቃለያ</u> ከዘመነ ሐዋርያት ቀጥሎ የተነሡ ሐዋርያውያን አበው ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ከሐዋርያት
ና ከአርድእት ያገኙአቸውን መጻሕፍት ተርጉመዋል። በሌላ በኩል በቅዱሳን ሐዋርያት እና አርድእት
ስም የተጻፉትን የሐሰት ወንጌላት ለይተው ከቤተክርስቲያን አውጥተዋል። መጽሐፍት ቅዱሳትን አጣመ
ው የተረጎሙ፣ ሐሰትን፣ ኑፋቄን፣ ክህደትን በቃልና በመጽሐፍ ያስተማሩትን የመንፈስን ሰይፍ ታጥቀው
በእግዚአብሔር ቃልተዋግተዋል። በውስጥ ይህንን የመሰለ ተጋድሎ ከማከናወናቸው በተጨማሪ በው
ጪ ካሉአላውያን ነገሥታት እሳቱን፣ ስለቱን ታግሰው የሕይወትና የአካል ዋጋ ከፍለው ተጋድሎአቸው
ን አጠናቀዋል። የውጭና የውስጥ ባላጋራ ያልበገራቸው ሐዋርያውያን አበውንመልዕክት፣ ትምህርት፣
ትርጓሜ መልስ የያዙት መጻሕፍተ ሊቃውንት ለዛሬው ትውልድም ሆነ ወደፊት ለሚነሣው ትውልድ እ
ጅግ አስፈላጊዎች ናቸው። መጽሐፍትን ለመተርጎም አበው ለመናፍቃን መልስ የሰጡባቸው መጻሕፍት
አስፈላጊዎች ናቸው። በመጻሕፍት ቤት ትርጓሜ ማዕከላት እነዚህ መጻሕፍት ዋጋቸው እጅግ የከበረ
ነው።

ቤተክርስቲያን ምስራቅ እና ምእራብ ተብላ በሥልጣን ጥመኞች እና ቅን ሐሳብ በጎደላቸው መ
ሪዎች ምክንያት በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስክትከፈል ድረስ የተጻፉት መጻሕፍተ ሊቃውንት
እውነተኞችና የቡድን መልክት ያላዘሉ በመሆናቸው በዓለም ሁሉ ባለችው ቤተክርስቲያን ዘንድ ተቀባ
ይነታቸው እንደተጠበቀ ነው። መጻሕፍተሊቃውንትየሚባሉትም በሃይማኖተ አበው የተጠቀሱት ሊቃው
ንት ለምሳሌ እነ ቄርሎስ፣እና አትናቴዎስ፣ ዮሐንስ አፈወርቀ፣ ጎርጎርዮስ፣ ባስልዮስ፣ ወዘተ የጻፉአቸ
ው መጻሕፍት የተረጎሙአቸው ትርጓሜያት ሲሆኑ በቤተክርስቲያን ሃይማኖተ አበው ተብሎ በሚጠራው
መጽሐፍ በከፊል ተሰባስበው ለንባብ በቅተዋል። በጉባኤ ቤት የታወቁት የሊቃውንት መጻሕፍት ሃይማ
ኖተ አበው፣ መጻሕፈ ቄርሎስ፣ ተረፈ ቄርሎስ፣ ድርሳነ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ተግሳጸዮሐንስ አፈወርቅ፣
ቅዳሴያት፣ ቅዳሴ ማርያም፣ እና ሌሎችም ናቸው። የመጻሕፈተ ሊቃውንት አስተምሮአቸው በአጠቃላ

ይ ከላይ እንደተጠቀሰው ምሥጢረ ሥጋዌና ምሥጢረ ሥላሴ ሲሆን ሌሎችም እነ ምሥጢረ ትንሣኤ ን የመሰሉት ዋና ዋናየሆኑ የሃይማኖት ትምህርቶች ተብራርተው ተገልጸውባቸዋል።

የአባቶቻችን በረከት፣ ጸሎት አይለየን።

አዘጋጅ መምህር ልዑለ ቃል አካሉ

ምንጭ

1. ሃይመኖተ አበው ግዕዝና አማርኛ። ትንሣኤ ዘጉባኤ 1986።
2. መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝበገ ቃለት ሐዲስ። ኪዳነ ወልድ ክፍሌ
3. የቤተክርስቲያን አስተምህሮ ትላንት፣ ዛሬ፣ ነገ። መምህር ልኡለ ቃል አካሉ። ገና ያልታተመ።